+++ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**+++**

#መቼ_ትመጣለህ **?**

መቼ ትመጣለህ**?** ነገ ወይስ ዛሬ**?**

በኃጢአት አልክበር ፤ ዕድሜዬን አልጨርስ ፤ አልብላው መንዝሬ።

ንገረኝ ጊዜውን ፤ ቆሜ ልጠብቅህ ፣

ግራ ቀኝ አልባክን ፤ እንዴት ነው አመጣጥህ ?

ትዘገይ እንደሆን ፤ ላትጠራኝ ቶሎ ፣

ከእፀ በለስ ልብላ ፤ ስሜቴ ገንፍሎ ፣

ምክንያቴን አብዝቼ ፤ አግዝፌ ልቆይህ ፣

ሔዋን አስታኝ ነው ፤ ሰይጣን አሳስቷት ፤

መከሯት ነው ልበልህ።

ለሥጋዬ ልስጣት ፤ ሥልጣኑን በሙሉ ነፍሴን ትበድላት ፣

ለጊዜው ትጠቀም ፤ አንተ ከዘገየህ ትሁነው እንዳሻት ።

ጊዜ አገኝ እንደሁ ፤ በተራገምኩበት መመረቅ እንድችል ፣

እስከ ጊዜው ድረስ ፤ ነፍሴ ታንጎራጉር ትንደደው ትቃጠል ።

ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ፤ ይኸው በዚህ ሰሞን ታሪክ ያወራሉ ፣

ያ! ስምንተኛው ሺህ ፤ ከተነገረ እንኳ ቆይቷል እያሉ

ሰዉ ጽድቁን ትቷል ሁሉም በያለበት ህሜቱን ቀጥሏል ፣

መጋደል መጣለፍ ፤ መቋሰል መቧደን ዝርፊያውም በርክቷል ፣

እንኳን ዳግም ም'ጻት የዓለም ፍጻሜ ስምህ ተዘንግቷል።

መቼ ትመጣለህ ነገ ወይስ ዛሬ**?**

ግዴለም ንገረኝ ፤ ልክ እንደኖኅ ጊዜ ዘመኑን አሰላና፣

ሃያዋ ብትበቃኝ ለንሰሓ ጊዜ ፤ በመቶው ልዝናና።

ገና አልበረደኝም ሰውነቴ ግሎ ውስጥ አካሌ ዘንቶ፣

ዓለሙን ያስሳል ፤ አንተ ከዘገየህ ለምን ሥራ ፈትቶ።

እበላው እንደሆን የሰበሰብኩትን ፤ ከሌላው ዘርፌ፣

እኖረው እንደሆን እንደማቱሳላ እድሜዬን አትርፌ።

ሺህ ዓመቴን ወስደህ ፤ የአንተን አንድ ቀን ትሰጠኝ እንደሆን ፣

ምናለበት ብዘርፍ ምናለ ብዘሙት ፤ መዘግየትህ ላይቀር ።

ከምድር እስከ ሰማይ ፤ ተዘርግቶ 'ማያልቅ ለበዛው ኃጢአቴ ፣

ጊዜ ካበደርከኝ እንዲሰረዝልኝ ፤ እንዲፋቅ ጥፋቴ ፣

ልክ እንደ ኢያሱ ፤ ፀሐይን አቁመህ ከጠበቅኸኝ በቃኝ ፣

ዛሬን ልዝናናበት ፤ ኃጢአት ልጨማምር ጨለማ ሳይወርሰኝ ፣

ይኸው ሰዉ ሁሉ ነገሩን ዘንግቶ ፤ ሁሉ ሆድ ብሶታል ፣

"ይዘገያል " አሉ እያለ ያወራል ፤ ኃጢአት ይሸምታል።

እኔም በቀደም 'ለት ፤ ከደጀ ሰላሙ ብዙ ጉድ አይቼ፣

ገዛሁት በርካሽ ፤ ኃጢአትን ከደጅህ ፤ ከቤትህ አግኝቼ።

ግዴለም ንገረኝ ፤ ሃያው ይበቃኛል በሌላውስ ላትርፍ ፣

እንዴት ከሌላው ህዝብ ፤ እኔ ተለይቼ እንደ ጅል ልንከርፈፍ ?

መቼ ትመጣለህ ነገ ወይስ ዛሬ**?**

ሌላውን ልበድል ፤ ነገርን ልዶልት ህዝብህንም ልቁጠር ፣

ከድንኳን ደጃፍ ፤ ተቀምጬ ላሹፍ ፤ ዘፈን ላንጎራጉር ።

ጊዜ ከሰጠኸኝ ፤ የምለይበትን ዘፈንን ከመዝሙር ፣

ንሰሐ ገባለሁ ልክ ስትመጣ ፤ ዛሬን ግን ልጨፍር።

ከጥብርያዶስ ባሕር ፤ ኃጢአት ዓሣን ላጥምድ፣

ትዘገይ እንደሆን ምናል ይህን ብትፈቅድ?

ይኸው ሰዉ ሁሉ ፤ ግራ ያጋባኛል ነገር እያማታ ፣

ኃጢአትን አግብቶ ፤ ትዳርን መስርቶ ጽድቅን እየፈታ ።

በክፋት ላይ ክፋት ፤ በዚያ ላይ ስምህን በፍፁም ደርቦ ፣

ጽድቅና ኃጢአትን ባንድ እያካሄደ በደስታ ተከቦ ፣

ጻድቅ ሲሸማቀቅ አንገቱን ሲደፋ ፤ ተመልካችም ሲያጣ ፣

እንዳሻው በመሆን ፤ ኃጥእ ሲዝናናበት ሲስቅ በለበጣ ።

ዘመናት አለፉ ፤ ይኸው ዛሬም የስምህ አጥፊዎች፣

ሥራቸውን ሰደው ፤ በደንብ ተስፋፍተው ዙሪያውን ብዙዎች ፣

ከደሃው ላይ ሰርቀው ፤ ምስኪን አስለቅሰው ለታቦት ሲያገቡ ፣

ወገን ጦሙን አድሮ ፤ ሲበሉ ሲጠጡ ሲያገቡ ሲጋቡ ።

እንኳንስ መምጣትህ ፤ ስምህ ተዘንግቶ አዳሜ ሲጨፍር ፣

እኔስ ምን ተዳዬ ፤ ከዚህ ህዝብ መሃል ተለይቼ ልቅር ?

ይልቅስ ንገረኝ ፤ ትመጣ እንደሆን ፀሐይ ሳትገባ ፣

አሊያም ልደባለቅ ከምድር ወገኖቼ ፤ ከወጣው ወጥቼ ከገባው ጋር ልግባ ።

 መቼ ትመጣለህ ነገ ወይስ ዛሬ**?**

የበራፌ ጥላ ከበር እስኪከተት ፤ 'ማትመጣ ከሆነ፣

አሸንክታብ ላርዝም ክብሬንም ልፈልግ ፤ ጊዜዬ ባከነ ፣

ዓለሙን ልከተል የዛሬን ልደሰት ፤ ነገ እመለሳለሁ ፣

አንተ ዛሬ ትመጣ ፤ ወይም እንደምትቀር በምን ዐውቀዋለሁ ?

ይኸው በዚህ ሰሞን ፤ ሰዎቹ በሙሉ ታሪክ ያወራሉ፣

እሱ ቀርቷል ብለው፣ ባንተም ላይ ደርበው ጣዖት ያመልካሉ።

ይኸው በዚያ ሰሞን ፤ ሥጋ ቤቱ ደጃፍ ሁሉ ተኮልኩሎ ፣

በሁዳዴ ምድር ቁርጥ ያወራርዳል ፤ መስቀል አንጠልጥሎ ።

እኔስ አያምረኝም ? አንተ እንደው አትመጣ ፤ ብበላ ምናለ ፣

ጠበል እረጫለሁ ፤ ወደፊት ጾማለሁ አንተ ከዘገየህ ፣

እንዲሁ በከንቱ ጊዜ ከሚባክን ፤ ቅዳሴ አስቀድሼ ዳንኪራ ቤት ብሄድ

ጽድቅን እንደሆነ ፤ መቼም አላጣትም ለኃጢአት ብሰደድ ፣

የልቤ ግድግዳ ቢጠቁር በክፋት ፤ ደግሞም ቢበሰብስ ፣

ዛሬ አንተ ካልመጣህ ነገ እታጠባለሁ ፤ ንስሐ ሳሙና እስካለልኝ ድረስ!

ምናለ ብሳደብ ሌላውን ብጎዳ ፤ ማንም እናዳይነካኝ ፣

ግዴለም ለነገ ግራዬን ቢያጮሉኝ ፤ ቀኜን ሰጣለሁኝ።

እንደ ሕፃን በርሬ ያሻኝ ቦታ ልድረስ ፤ ያሻኝን ልተንፍስ ፣

አኩኩሉ ልበል ፤ በኃጢአት ጫካ እስክትመጣ ድረስ ።

   መቼ ትመጣለህ ነገ ወይስ ዛሬ**?**

ምናለ እንደ ዴማስ ፤ ይህችን ዓለም ብወድ አንዴ ብተፈቅድልኝ ?

በኋላ መጣለሁ ልክ እንደ ድሮዬ ፤ አገለግላለሁ ቆመህ ከጠበከኝ።

ትዘገይ እንደሆን ፤ በቶሎ ማትመጣ አሊያ የምትቀር ፣

ምናል ሳማ ሰንበት ፤ ብሄድ ለሽርሽር ?

ቢራዬን ገዝቼ ፤ ቱታዬን አጥልቄ ፣

ልክ እንደ ቱሪስቶች ፤ ምግቤንም ሰንቄ ፣

በውጭዎች ፈሊጥ ፤ እየተቀናጣሁ ደርሼ ብመለስ፣

ምናለ ባልጸልይ ፤ ምናል ባላስቀድስ ?

ይኸው ትናንት እንኳ ፤ ትናንትና ማታ

ሰዎች ተኮልኩለው ፤ ከዐውደ ምሕረቱ ፣

አየሁኝ ሲጣሉ ፤ በቡድን ተከፍለው ነገር ሲዶልቱ።

እኔስ ምን አለበት ፤ በነሱ ብጽናና በኃጢአት ባድግ፣

አንተ እንደሁ አትመጣ ፤ ስንት ዘመን ሆነኝ ቆሜ ሳደገድግ ።

ፍጹም ልመሳሰል ከዚህ ዓለም ጋራ ፤ ማንነቴ ጠፍቶ ፣

አንተ ከዘገየህ ፤ ምናል ይህ አካሌ ቢኖር ሕይወት አጥቶ ?

ጊዜዬን ልስራበት ለኃጢአት ልነሣ ፤ ለጽድቅህም ሞቼ ፣

ክርስትናው እንደው መቼም አይቀርብኝ ፤

ነገ እቆርባለሁ በምርኩዝ መጥቼ ።

መቼ ትመጣለህ ነገ ወይስ ዛሬ?

ይኸውና ዛሬ ሁሉ ቀላል ሆኖ ፤ መፈራትህ ጠፍቶ ፣

የነዲዮስቆሮስ የነጴጥሮስ እምነት ፤ ከኋላ ተገፍቶ፣

ሰው ሰውን እያየ በሥጋ ሲጽናና ፤ አምላክን ረስቶ ፣

ከዐውደ ምሕረቱ አንተ ተሸፍነህ ፤ እኔን ስሙኝ በዝቶ ፣

እምነት እንደፋሽን ራሱን ተኩሎ ፤ ራሱን ቀብቶ ፣

በደፋሮች ጩኸት መቅደስህ ታውኮ ፤ መቅደስህ ሲረክስ ፣

ዐዋቂ አንገቱን በደፋበት መድረክ ፤ ታዋቂ ሲነግሥ።

ነጠላና ቀሚስ የጽድቅ መገለጫ ፤ በሆኑበት ዘመን፣

በስሜት ተነድቶ በስም ብቻ ሲሮጥ ፤ ህዝብህም ሲባዝን ፣

እኔስ ምን ተዳዬ ፤ ለግዜው ብደሰት ?

ሆ! ካለው ሆ ብዬ አብሬው ብዘምትም ፤ ሆሳዕና ብዬ ዛሬ ብዘምርም ፣

ከሳምንት በኋላ በዚያው አንደበቴ ፤ ይሰቀል !ይሰቀል! ማለቴ አይቀርም ።

እምነቱ ባይገባኝ ፤ እኔ ምን አገባኝ ?

ዝም ብዬ ሮጣለሁ

ምን ችግር አለበት አንተ ከዘገየህ ፣ ምስጢረ ሥላሴን ውዳሴ ማርያምን ፤

ቀስ ብዬ እማራለሁ ፣

አንተ እንደ ምትመጣ ፤ ወይ እንደ ምትቀር በምን ዐውቀዋለሁ ???????